የሰ/መ/ቁ. 241920
ጥቅምት 02 ቀን 2016 ዓ.ም.

ዳኞች፡-

ተፈሪ ገብሩ (ዶ/ር)

እንዳሻው አዳነ

ተሾመ ሽፈራው

መላኩ ካሳዬ

ነጻነት ተገኝ

አመልካች፡- አቶ አብዱራዛቅ ሱልጣን

ተጠሪ፡- 1. አቶ ደረጀ ሱልጣን - ቀርበዋል

2. ወ/ሪት ዘቢባ ሱልጣን - ቀርበዋል

መዝገቡ የተቀጠረው መርምሮ ፍርድ ለመስጠት ነው፡፡ በመሆኑም መርምረን የሚከተለውን ፍርድ ሰጥተናል፡፡

ፍርድ

ይህ የሰበር አቤቱታ ሊቀርብ የቻለው አመልካች የካቲት 03 ቀን 2015 ዓ.ም ጽፈው ባቀረቡት የሰበር አቤቱታ የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ 297305 በጥር 18 ቀን 2015 ዓ.ም የፌደራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁ 100029 ጥቅምት 14 ቀን 2015 ዓ.ም በማጽናት የሰጠው ትእዛዝ ስህተት የተፈጸመበት ስለሆነ በሰበር ታይቶ ይታረምልኝ በማለታቸው ነው፡፡

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ለነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ
ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

ጉዳዩ ልጅነትን መካድ የሚመለከት ሆኖ ክርክሩ የተጀመረው በፌደራል መጀመሪያ ደረጃ ፍ/ቤት ነው፡፡ በስር ፍ/ቤት አመልካች የመቃወም አመልካች ሲሆን ተጠሪዎች ደግሞ የመቃወም ተጠሪዎች ነበሩ፡፡ አመልካች ሚያዝያ 5 ቀን 2014 ዓ.ም በተጻፈ አቤቱታ 1ኛ ተጠሪ የተሰጣቸው የልጅነት ምስክር ወረቀት ውሳኔ እንዲሰረዝ የሰው ምስክር በማስረጃነት በማቅረብ ጠይቀዋል፡፡

1ኛ ተጠሪ ባቀረቡት መልስም ልጅ ስለመሆናቸው የልደት የምስክር ወረቀት የተሰጣቸው መሆኑን ፤ፍ/ቤቱም ይህንን ማስረጃ መሰረት አድርጎ ውሳኔ የሰጠ በመሆኑ የተሰጠው የልጅነት ማስረጃ ሊጸና ይገባል በማለት ተከራክረዋል፡፡

ጉዳዩ የቀረበለት ፍ/ቤትም የግራቀኙን ክርክርና ማስረጃ ከመረመረ በኃላ አመልካች ባቀረቧቸው ምስክሮች 1ኛ ተጠሪ በእርግጥም ልጅ አለመሆኑን አላረጋገጡም በአንጻሩ 1ኛ ተጠሪ ባቀረቡት የልደት የምስክር ወረቀት እና የሰው ምስክሮች የልጅነት ሁኔታ መኖሩን አስረድተዋል በማለት ለ1ኛ ተጠሪ የተሰጠው የልጅነት ማስረጃ ሊሰረዝ አይገባም ሲል ወስኗል፡፡

አመልካች በዚህ ውሳኔ ቅር በመሰኘት ይግባኛቸውን ለከፍተኛ ፍ/ቤት ያቀረቡ ቢሆንም ፍ/ቤቱ አቤቱታውን በፍ/ሥ/ሥ/ህ/ቁ 337 መሠረት ሰርዞታል፡፡

አመልካች የካቲት 03 ቀን 2015 ዓ.ም ጽፈው ያቀረቡት የሰበር አቤቱታ ይህን ውሳኔ በመቃወም የቀረበ ሲሆን ይዘቱም አመልካች 1ኛ ተጠሪ የአባታቸው ልጅ አለመሆኑን ካቀረቡት የሰው ማስረጃ በተጨማሪ የዲ.ኤን.ኤ ምርመራ እንዲደረግ ፍ/ቤቱን ጠይቀው ፍ/ቤቱ ምርመራው እንዲደረግ ትእዛዝ ሳይሰጥ ውሳኔ መስጠቱ ስህተት መሆኑን፤ ፍ/ቤቶች በተከራካሪ ወገን የሚቀርብላቸውን የዲ.ኤን.ኤ ምርመራ ማለፍ እንደሌለባቸው የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁጥር 152719፣90121 እና በመ/ቁጥር 116119 አስገዳጅ ውሳኔ የሰጠ መሆኑን፤ 1ኛ ተጠሪ ያቀረባቸው ምስክሮች ከሚች እንደተወለደ ከሰው ሰማን ከማለት ውጪ መቼ ከማን ተወለደ የሚለውን እና እናቱ ማን እንደሆኑ እንደማያወቁ መስክረው እያለ እንዲሁም አመልካች ያቀረቧቸው ምስክሮች 1ኛ ተጠሪ የሚች ልጅ አለመሆኑን መስክረው እያለ የስር ፍ/ቤት ለሰሚ ሰሚ ምስክር ቦታ ሰጥቶ የአመልካችን ምስክር ቃል ዋጋ በማሳጣት የማስረጃ ምዘና ስህተት ፈጽሟል የሚል ነው፡፡

የአመልካች የሰበር አቤቱታ በሰበር አጣሪው ችሎት ተመርምሮ የ1ኛ ተጠሪ የልጅነት ጉዳይ በሁኔታ የሚረጋገጥ ከሆነ የ DNA ምርመራ ሳያደርግ ውሳኔ ላይ የተደረሰበት አግባብ ለማጣራት የሚል ማስቀረቢያ ጭብጥ በመያዝ ተጠሪዎች መልስ እንዲሰጡበት ተደርጎ ጉዳዩ ለዚህ ችሎት ቀርቧል፡፡

1ኛ ተጠሪ ግንቦት 18 ቀን 2015 ዓ.ም ጽፎ ያቀረበው መልስ ይዘትም አመልካች የሚች አቶ ሱልጣን ጣሂር ልጅ ስለመሆናቸው በፍ/ቤት ያላረጋገጡና የልደት ምስክርም ያላቀረቡ በመሆኑ አቤቱታቸው ውድቅ ሊደረግ ይገባል የሚል የመጀመሪያ ደረጃ መቃወሚያ እና የፍሬ ነገር መልስ ያቀረቡ ሲሆን በመልሳቸውም አመልካች ከሚች ከጋብቻ ውጪ የተወለዱ በመሆናቸው እና የሚች ልጅ ስለመሆናቸው ያቀረቡት ማስረጃ ስለሌለ 1ኛ ተጠሪ የሚች ልጅ አይደለም በማለት የ DNA ምርመራ እንዲደረግ መጠየቅ የማይችሉ መሆኑን፤ ሚች በህይወት እያሉ 1ኛ ተጠሪን ልጄ ነው ብለው ተቀብለው ከሌሎች ልጆቻቸው ጋር ያስተዋወቋቸው እና በአካባቢው ማህበረሰብ ዘንድም ልጅ መሆናቸው የሚታወቅ በመሆኑ አባታቸው ሳይቃወሙ አመልካች መቃወማቸው ተገቢ አለመሆኑን፤ የስር ፍ/ቤትም የምስክሮችን ቃል በአግባቡ መዝኖ ውሳኔ ሰጥቷል የሚል ነው፡፡

2ኛ ተጠሪም ግንቦት 18 ቀን 2015 ዓ.ም ጽፈው ባቀረቡት መልስ 1ኛ ተጠሪ ሚች በህይወት እያሉ በጋብቻ ውስጥ ከተወለዱ ልጆቻቸው ጋር ያስተዋወቋቸው እና ሚችም ልጅ መሆኑን የተቀበሉ በመሆኑ የስር ፍ/ቤት ውሳኔ ተገቢ ነው የሚል ነው፡፡

አመልካች ሰኔ 16 ቀን 2015 ዓ.ም የተጻፈ የሰበር አቤቱታቸውን የሚያጠናክር የመልስ መልስ አቅርበው ከመዝገቡ ጋር እንዲያያዝ ተደርጓል፡፡

የጉዳዩ አመጣጥ በአጭሩ ከላይ የተገለጸው ሲሆን ይህ ችሎትም የግራ ቀኙን ክርክር ለሰበር አቤቱታው መነሻ ከሆነው ውሳኔ፣ ለጉዳዩ አግባብነት ካላቸው ድንጋጌዎች እና ቅሬታው ለሰበር ያስቀርባል ሲባል ከተያዘው ነጥብ ጋር በማገናዘብ እንደሚከተለው መርምሮታል፡፡

በመሠረቱ ስለልጅነት ቀዳሚ ማስረጃ የልደት ምስክር ወረቀት ስለመሆኑ የተሻሻለው የቤተሰብ ሕግ አዋጅ ቁጥር 213/92 አንቀጽ 154 የሚያስገነዝብ ሲሆን የልደት ምስክር ወረቀት በሌለ ጊዜ የልጅነት ሁኔታ መኖሩን በመስረዳት ልጅነት ለረጋገጥ እንደሚችል በአንቀጽ 155 ተመልክቷል፡፡ የልጅነት ሁኔታ መኖር የሚለው ትርጉም ደግሞ አንድ ሰው በማህበረሰቡ ዘንድ የእርሱ ወይም የእርሷ ልጅ ነው እየተባለ የሚገመት ስለመሆኑ በአዋጁ አንቀጽ 156 ስር በግልጽ ተቀምጧል፡፡ ስለሆነም በዚህ አኳኋን የልጅነት ሁኔታ መኖሩን ለማስረዳት የተቻለ እንደሆነ ፍርድ ቤቱ ልጅ ነው ሲል የሕግ ግምት አንደሚወስድ፣ሆኖም ይህ የሕግ ግምት ልጁ የተባለው ሰው ልጅ ሊሆን እንደማይችል በማረጋገጥ ሊፈርስ እንደሚችል በአንቀጽ 157(1) እና (2) ስር እንደቅደም ተከተሉ ተመልክቷል፡፡

በተያዘው ጉዳይ የስር ፍርድ ቤት የ1ኛ ተጠሪን የሚች ልጅነት ለማስረዳት ከቀረቡት ማስረጃዎች ለውሳኔው መሰረት ያደረገው በቀዳሚ ማስረጃነት ተቀባይነት ያለውን የልደት የምስክር ወረቀት ሲሆን በተጨማሪም የልደት የምስክር ወረቀቱ እያለም የቀረቡት ምስክሮች በመስማት የልጅነት ሁኔታ መኖሩን አስረድተዋል በማለት ነው፡፡ በዚህ ደረጃ 1ኛ ተጠሪን የሚች ልጅ ነው የሚል የሕግ ግምት ለመውሰድ የሚያስችል ቢሆንም በአመልካች በቀረበው መቃዋሚያ 1ኛ ተጠሪ ልጅ አይደለም የሚሏቸውን ምክንያቶች እና ምስክሮች ከማቅረባቸው በተጨማሪ ፍርድ ቤቱ የዲ.ኤን.ኤ ምርመራ እንዲደረግ በማድረግ እንዲወሰን ጠይቀዋል፡፡

የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎት በመ/ቁ 62041 ላይ አባትነት በፍርድ ሊነገር በሚችልባቸው ሁኔታዎች ላይ ሳይንሳዊ የደም ምርመራ ዲ ኤን ኤ በማስተባበያ ማስረጃነት ሊቀርብ የሚችል በመሆኑ በዚህ ረገድ ተከራካሪ ወገኖች የሚያቀርቡትን አቤቱታ ፍርድ ቤቶች በአግባቡ ማስተናገድ ያለባቸው ስለመሆኑ አስገዳጅ የሕግ ትርጉም ሰጥታል ፡፡ ይህም 1ኛ ተጠሪ የሚች ሱልጣን ጣሂር ልጅ ናቸው በማለት ያገኙትን የሕግ ግምት በአንቀጽ 157(1) (2) እንደተመለከተው የሚች ሱልጣን ጣሂር ልጅ ሊሆን እንደማይችል በማረጋገጥ ሊፈርስ የሚችል በመሆኑ አመልካች ይህንን ለማስተባበል በዲ.ኤን.ኤ ምርመራ እንዲደረጋገጥ ያቀረቡ ሆኖ ሳለ የስር ፍርድ ቤት ሳይመረምር ወይም ያልተቀበለም ከሆነ ሳይገልጽ በአመልካች የቀረቡትን የሰው ምስክሮች ብቻ በመመዘን ውድቅ በማድረግ የደረሰበት ድምዳሜ መሆኑን የስር ፍርድ ቤት መዝገብ ያስገነዝባል፡፡ ይህ በይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤትም አልታረመም፡፡

ስለሆነም የሥር ፍርድ ቤት በአመልካች የቀረበውን የዲ.ኤን.ኤ ምርመራ አቤቱታ በማለፍ የቀረበውን የልደት የምስክር ወረቀት እና በግራ ቀኙ የቀረቡትን የሰው ምስክሮች በመመዘን የሰጠው ውሳኔ መሰረታዊ የህግ ስህተት የተፈጸመበት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡ በዚህም መሰረት ተከታዩን ተወሰነ፡፡

ውሳኔ

1. የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመ/ቁ 297305 በጥር 18 ቀን 2015 ዓ.ም የፌደራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በመ/ቁ 100029 ጥቅምት 14 ቀን 2015 ዓ.ም በማጽናት የሰጠው ውሳኔ በፍ/ብ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 348/1/ መሠረት ተሽሯል ፡፡

ማስታወሻ፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ለነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !

2. የፌደራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በአመልካች የቀረበውን የዲ.ኤን.ኤ ምርመራ አቤቱታ ላይ ተገበውን ትእዛዝ በመስጠት የሚቀርብለትን ማስረጃ በመመርመር ውሳኔ እንዲጥበት በፍ/ሥ/ሥ/ሕ/ቁ 343/1/ መሰረት መልሰን ልከናል፡፡

3. አመልካችና ተጠሪ በዚህ ችሎት ለተደረገው ክርክር ያወጡትን ወጪና ኪሳራ ይቻቻሉ፡

4. የስር ፍ/ቤት መዝገብ ተመላሽ ይሁን፡፡

<u>መዝገቡ ተዘግቷል</u>፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት

ፅ/ወ

<u>ማስታወሻ</u>፡- ይህ የሰበር ችሎት ውሳኔ ለነድ ለጥናትና ምርምር ሥራ ወይም ለግንዛቤ እንጂ

ለፍርድ አፈጻጸም ዓላማ አያገለግልም !